የፍትሐብሔር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

የተዋረድ መዋቅሩን ጨምሮ ከተሰጡት በርካታ ተግባር እና ሃላፊነቶች መካካል ዋና ዋናቹ የክልሉ ህዝብና መንግስት መብትና ጥቅሞች ሕጋዊ ወኪል በመሆን የመደራደር፣ የመከራከር፣የማስከበር፣እንዲከበሩ የማድረግ፣ የሚከበሩበትን ሂደት የመከታተል እና የመቆጣጠር፣ የክልሉ መንግስት ተቋማት ሃብትና ንብረት ያላግባብ እንዳይባክንና እንዳይመዘበር ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ፣ የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች የውል ግዴታ ለመግባት የሚያግዝ ረቂቅ ውል የማዘጋጀት፣ተዘጋጅተው የቀረቡ ረቂቅ የውል ሰነዶችን መርምሮ አስፈላጊውን መመሪያ የመስጠት፣እንደ አስፈላጊነቱ ተዋዋይ ወገኖች ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው በግንባር ቀርበው ወይም በውል ሰጭ መስሪያ ቤት ውል አስተዳደር ክፍል እንዲፈራረሙ የማድረግ፣ በክልሉ መንግስት ፕሮጀክቶችና በሌሎች ጉዳዮች ጭምር የውል ሰነዶች ዝግጅትና ድርድር የማድረግ ወይም የሚመለከታቸውን አካላት የማማከር፣ ከክርክር በፊትም ሆነ በኂላ እንዲሁም በክርክር ወቅት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመንግስት ተቋማት ምክር የመስጠት፣አቅጣጫዎችን የማሳየት እና በሕግ መሠረት ውሳኔዎችን የማስፈጸም፣በሚቀርቡ የፍትሐብሔር መዛግብት ላይ አዋጭ አለመሆኑ ከታመነበት ክስ፣ ይግባኝ፣ የሰበር አቤቱታ አይቀርብም ውሳኔ የመስጠት፣የስር ዐቃቤ ሕግ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ውሳኔውን መርምሮ የማጽናት፣የመሻር ወይም ተለዋጭ ትዕዛዝ የመስጠት፣ በየደረጃው ያለ ዐቃብያነ ሕግ በትይዩ ባሉት ፍርድ ቤቶች በከሳሽነት፣ በተከሳሽነት፣ በይግባኝ ባይነት፣በይግባኝ መልስ ሰጭነት፣በሰበር አመልካችነትና በሰበር ተጠሪነት ጉዳዮችን ይዞ የመከራከር ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ደራጀውን( ትይዩውን) ሳይጠብቅ በማኛውም ፍርድ ቤትና የዳኝነት ሰሚ አካል ቀርቦ የመከራከር፣ዝርዝሩ አዋጅ ቁጥር 280/2014ን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የክልሉ መንግስት መስሪያቤቶች አንዱ ከሌላው ጋር ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ያጋጠሙ እንደሆነ እርስ በርስ በማደራደር ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ጥረት የማድረግ እና መስማማት ካልቻሉ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት፣በልዩ የስራ ጠባያቸው ምክንያት የራሳቸው ነገረ ፈጅ ካላቸው መስሪያቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ውጭ ያሉትን ክልላዊ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በመወከል በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች፣ በማንኛውም የዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባኤ ክስ የማቅረብ፣ሲከሰሱም መልስ የመስጠት፣የመደራደር፣የመከራከር፣በልዩ ሁኔታ ነገረ ፈጅ ያላቸው የመንግስት ተቋማት እና የልማት ድርጅቶች ተከራካሪ በሆኑባቸው

ጉዳዮች የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን የማድረግና የሕግ ድጋፍ ሲጠይቁ እገዛ የማድረግ፣በሕግ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በሆኑ ጉዳዮች የህብረት ስራ ማህበራትን በመወከል ሲከሱም ሆነ ሲከሰሱ የመከራከር ፣የመደራደር፣እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የሕግ ድጋፎችን የማድረግ፣ በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው እና ገንዘብ ከፍለው ለመከራከር ለማይችሉ አቅም የሌላቸውን ሰለባዎች፣የአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን፣ደሃ ሴቶችን፣አካል ጉዳተኞችን፣አረጋውያንን፣የኤች አይቪ ኤዲስ ህሙማንን፣ ወክሎ በድርድር ወይም በፍርድ ቤት እና በሌሎች የዳኝነት ሰሚ አካላት ዘንድ በመከራከር ካሳ እንዲያገኙ እና የፍትሐብሔራዊ ነክ ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩ የማድረግ፣ በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና በሌሎች የሕግ ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው አቅም የሌላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል በሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮች ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ጥረት የማድረግና በድርድር ለመፍታት ያልተቻለ እንደሆነ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ጉዳይ ይዞ የመከራከር እና የሕግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች ጉዳይ ለጠበቃ እንዲመራ የማድረግ፣ለክልላዊ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የሕግ ድጋፍ የማድረግ ፣ለፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የተከሳሽ/የፍርድ ባለዕዳን ገንዘብ /ንብረት/ በስጦታ፣በሽያጭ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ እንዲታገድ የማድረግ፣ከህግ ውጭ ጋብቻ እንዳይፈጸም የመከላከል እና ተፈጽሞ ሲገኝም በሕግ መሰረት ጋብቻው እንዲፈርስ የማድረግ፣በድርድርም ሆነ በፍርድ ባለመብት የሆነባቸውን ጉዳዮች የማስፈጸም ተግባር እና ኃላፊነት አለበት፡፡